# ቀስተ ደመና

የሰላምና የወድማማችነት ድምፅ ሬድዮ ጋዜጣ

ቁጥር 4- 6 ታህሣሥ / የካቲት 1990

## ከአዘጋጅ ብዕር

የቀስተ ደመና ሬዲዮ፤ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ ሥርጭቱን የጀመረው መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም ነው።

ይህ ሁለተኛ መጽሄት የሚቀርበው ሬዲዮው ከጀመረ ከስድስተኛው ወር በኋላ ስለሆነ በቅርቡ ከተላለፉትና ባጭሩ ከቀረቡት የተወሰኑ ዜናዎች ሌላ፤ የመጽሄቱ ዋና ይዘት ለሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ቅድሚያ ትኩረት ለሰጡ ትችቶች፤ ትንተናዎች ወዘተ ነው።

መልካም ንባብ !


* ክሊንተን አፍሪካ........................1
* የፖለቲካ አጥቂነት....................2
* በአንድ ራስ አንድ ምላስ.........3
* ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ኬንያ.......5
* የእብዶች ሎጂክ ........................6
* በ 1992ቱ ምርጫ ላይ የተጠነሰሰው ሤራ.....................7
* ህወሀት ለምርጫ ይዘጋጃል፤ ተቃዋሚዎችስ?.........................8
* የወያኔ መሰንበቻ ስልት...........10
* ከጋዜጦች አምድ.................... 11
* ዘመናዊ ባርነት...................... 15
* የወያኔን ኢትዮጵያ ሾላ በድፍን.......................17


ቀስተ ደመና (Radio Rainbow) የሰላምና የውንድማማችነት ድምፅ ሬዲዮ
በአጭር ሞገድ(short wave) እንደሚከተለው ይተላለፋል ፤

| ቀን | ሞገድ | ሰዓት | አቅጣጫ |
|---|---|---|---|
| ሐሙስ | 19 ሜትር ባንድ 15.365HZ | በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ 1 እስከ 2 ሰዓት | ምስራቅ አፍሪካ ኢትዮጵያ |
| ዓርብ | 31 ሜትር ባንድ 9855kHz | በአሜሪካ ሰዓት አቆጣጠር 9.00p.m. - 10.00pm | ሰሜን አሜሪካ ምስራቃዊ ጠረፍ |
| እሁድ | 49 ሜትር ባንድ 5.910kHz | በአውሮፓ ሰዓት አቆጣጠር 9.00a.m-10.00am (10.00-11.00a.m ለብሪታንያ ) | ምዕራብ አውሮፓ |

አድራሻችን፤
አስተያየት፤
ትችት፤ ወዘተ
ካላችሁ,


Radio Rainbow ,
c/o P.O .Box 140104
53056 Bonn , Germany
Fax : 0049 228 612381



GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA
Groupe de Recherche et d'Action pour la paix en Ethiopie et dans la Corne de l' Afrique
Research and Action Group for peace in Ethiopia and the Horn of Africa
ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

በአሁን ግዜ ከ 16 በላይ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ከህግ ውጭ በሆነ እሥራት ላይ የሚገኙ ሲሆን በዚሁም የጅምላ እስራት ምክንያት የተዘጉት የጦቢያ፤ የዑርጂ፤ የወንጪፍና ሌሎችም ጋዜጦች ሥራቸውን ሊቀጥሉ ያለመቻላቸው ታውቋል።

--------------////--------------

# የእብዶች ሎጂክ

የወያኔ ኢህአደግ መንግሥት አሥራ አምስት ቀን በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሶስት ጋዜጦች ከህትመት ውጭ እንዲሆኑ ከማድረግ አልፎ በነፃው ፕሬስ ላይ ቀደም ሲልም ተያይዞት የነበረውን የመንግሥታዊ የሽብር ዘመቻ ወደ አዲስ ምዕራፍ አሸጋግሮ የጋዜጦችን ጽ/ቤትና ንብረት በእሳት እስከማጋየት ደርሷል።

ወያኔ ወደዚህ አዲስ የሽብር ስልት ለምን እንደሸጋገረ ብዙ ታዛቢዎች ግራ ተጋብተዋል። ይህም ሆኖ ከአርብ ማታ ወዲህ ተደጋግመው የሚመጡ ሁለት ምክንያቶች አሉ። በአንድ በኩል የሃገሪቱ ውስጣዊ የፖለቲካና ወታደራዊ ሁኔታ ሲሆን ሌላው ደግሞ በመጋቢት አጋማሽ የአሜሪካኑ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንቶን ያደርጋሉ የተባለው ጉብኝት ጋር ያያይዙታል። እነዚህ ምክንያቶች በርግጥም እውነት ከሆኑ የወያኔ መሪዎች የተከተሉት የእብዶች ሎጂክ ነው ማለት ይቻላል።

የሃገሪቱን ውስጣዊ ሁኔታ ምክንያትነት እንመልከት። እርግጥ ዛሬ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽ እየሆነ የመጣው በአንድ በኩል በወያኔ ባራሱ ውስጥ ያለው ቅራኔና በሌላ በኩል ደግሞ ከእለት እለት እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ያለው ጸረ ወያኔ የሆነው የተቃዋሚ ኃይሎች ሁለገብ ትግል አለ። ይህ እንደ ምክንያት ከተወሰደ በእርግጥም ሕዝቡ ከሚጠረጥረውና ታዛቢዎች ከሚተነትኑት በላይ ሁኔታው አንዳንድ የወያኔ መሪዎች የሚይዙት የሚለቁት አሳጥቷቸዋል ማለት ነው። ነገር ግን ደግሞ ከዚህ ውጥረት ሽብርን በመፍጠር እንወጣለን ካሉ እነዚህ የወያኔ መሪዎች የሚከተሉት የእብዶች ሎጂክ ነው ከማለት ሌላ ምንም መጨመር አይቻልም። እንዲህ አይነቱ ድርጊት በወያኔ በራሱ ውስጥ ከአጥፍቶ መጥፋት ፖሊሲን በሚከተሉና ለሃገሪቱ ችግሮች ሰላማዊ፤ ዴሞክራሲያዊና የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የሚያስቀድሙ መፍትሄዎችን በሚሹት ኃይሎች መሃከል ያለውን ቅራኔ ያባብሰዋል እንጂ አያረግበውም። በጸረ ወያኔ ትግል በተሰማሩት ኃይሎችም አካባቢ የሚደረገውን ሁለገብ ትግል ይበልጥ የሞት ሽረት ተጋድሎ መልክ እየሰጠ ያጎለብተዋል እንጂ በምንም አይነት አያበርደውም።

ሁለተኛው የሚሰነዘረው ምክንያት የአሜሪካኑ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንቶን ያደርጋሉ የተባለው ጉብኝት ጋር የተያያዘ ነው። እንደነዚህ ታዛቢዎች ከሆነ የወያኔ አንዳንድ መሪዎች ዓላማ አቅፋ ደግፋ የያዘቻቸው የአሜሪካ መሪ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ቢያንስ በአዲስ አበባ ደረጃ ከተቃዋሚ የጸዳችና ነጻው ፕሬስ ህዝቡን መቀስቀስ የማይችልባት የተረጋጋች የምትመስል አገር ለማሳየት ይፈልጋሉ።

እንዲህ አይነቱ ሎጂክ ደግሞ ከእብደትም እብደት ነው።

**መጀመሪያ አንድ ጨርሶ እንግዳ የሚሆን ነገር አለ። በዓለም አቀፍ ደርጃ የነጻ ፕሬስ፤ የዴሞክራሲ፤ የሰው ልጅ መብት ግንባር ቀደም ተሟጋች ነኝ የምትል አገር መሪ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ባይሆን በጎደለ እንዲሞላ ጥረት ማድረግ ይጠበቃል እንጂ ለሳቸው እጅ መንሻ ሲባል ይህ መከረኛ ሕዝብ ከወትሮው ይበልጥ የሚንገላታበት፤ ድሮውንም በሞት አፋፍ ላይ የነበረው ነፃ ፕሬስ ሞቶ እንዲቀበር የሚደረግበት ስሌት ትክክለኛ አእምሮ ላለው ሰው ግልጽ አይሆንም።**

ሌላው ደግሞ እንግዲህ በአሜሪካኖች በራሳቸው በኩል የዚህን ነገር ቅራኔም አለመረዳት ሁኔታ ሊኖር ይችል ይሆናል። የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ሃገራችንን ሲጎበኙ በእሳቸውም ላይ ባይሆን በፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ላይ ምንም አይነት የተቃውሞ ሰልፍ እንደታሰበው

ባይደረግ፤ ከነጻ ፕሬስ በኩል ምንም ድምጽ ባይሰማ ይህንን አጉል ጸጥታ የተሳሳተ ትርጉም ሊሰጡት ይችሉ ይሆናል።

ይህ እንዳይሆን ከተፈለገ የሃገሪቱ ተቃዋሚ ኃይሎች የሚጠበቅባቸው ተግባር ግልጽ ነው። ይህና ምናልባትም እየተስፋፋ ለመሄድ የሚችለው መንግሥታዊ ሽብር ከታሰበው ጉብኝት ጋር ያለውን ግንኙነት አጉልቶ በማሳየት ዲፕሎማሲያዊውን ትግል ማፋፋምና ፕሬዚዳንት ክሊንተን ያሰቡትን ታሪካዊ ጉብኝት የኢትዮጵያ ሕዝብ በተረጋጋ መንፈስ ወዳጅ ለሆነው የአሜሪካን ሕዝብ ያለውን ፍቅርና ለመሪው ያለውን አክብሮት ሊገልጽ የሚችልበት ሁኔታ እስከመጣ ድረስ እንዲያስተላልፉ መጠየቅ ያስፈልጋል። ይህ የማይሳካ ከሆነ ግን ይህ ጉብኝታቸው የሚካሄደው በመንግሥታዊ ሽብር ብቻ የተረጋጋች የምትመስል አገር እንደሆነ ተገንዝበው ኢትዮጵያን ሳይሆን እነ መለስ ዜናዊን ጎብኝተው የሚመለሱ መሆናቸውን ከወዲሁ ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል።

--------------////--------------

## የ1992 ዓ ምን ምርጫ ለማጨናገፍ ሴራ መጠንሰሱ ተገለጸ

**ነጻውን ፕሬስ ለማጥፋት የተከፈተው አዲስ ዘመቻ የ1992 ዓ ምን ምርጫ ለማኮላሸት በኢህአዴግ የተጠነሰ ሰው ሤራ የመጀመሪያው ምእራፍ መሆኑን በአዲስ አበባ ያሚገኘው የቀስተ ደመና ሬዲዮ አንድ ተወካይ ከሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል።**

ወኪላችን ከተለያዩ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ያጠናቀረው ሪፖርት እንደሚያመለክተው ከሆነ እስካሁን ነጻና ርዕታዊ ምርጫን አሻፈረኝ በማለቱ ለባእድ ደጋፊዎቹ ሳይቀር አስቸጋሪ ሁኔታ የፈጠረው ኢህአዴግ የነዚህን ባእዳን ተቃውሞ ጋብ ለማድረግ መጭውን ምርጫ ካለፈው ከፊት ያለ ለማስመሰል እቅድ ያወጣ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ደርጃ በደረጃ እንዲከናወን የተጠነሰሰው ይህ ሤራ በግዜው ካልተጋለጠ ሀገሪቱ ከፍተኛ ፈተና ላይ ልትወድቅ ትችላለች በማለት የሚተቹትን ውስጥ አዋቂ ምንጮች የሚጠቅሰው ይህ ሪፖርት የሤራውን ይዘት እንደሚከተለው አቅርቦታል፤